# “ሰላማዊ (non-violent) ትግል”

**ከጥኡመልሳን አድማሱ**

*ምንም እንኳን ከዚህ በላይ በተመለከተውና በመሳሰሉት ኢትዮጵያ ነክ የመነጋገሪያ አርእስት ዙርያ በተነሱና በሚነሱት ውይይቶች በቅርብ የምከታተል ብሆንም እስከአሁን ድረስ በውጪና ባገር ውስጥ እንደሚኖረው ኣብዛኛው ኢትዮጵያዊ እንደሚያደርገው ኔታዎችን በአርምሞ ከመከታተል በስተቀር ያደረግሁት አስተዋፅኦ የለም።*

*ሌላው ቢቀር በሚነሱት ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ያለኝን አስተያየት እንደአቅሜ መሰንዘር እችል እንደነበር ባውቅም እስከአሁን ድረስ የነበረውን እድል ወይም አጋጣሚ አልተጠቀምኩበትም።*

*አሁንም ይህን አጭር ጽሁፍ ቢጤ እንዳቀርብ መነሻ የሆነኝ ከፍ ብሎ የተመለከተውን ርእስ መሰረት በማድረግ አቶ መክብብ ማሞ ያቀረቡት መጣጥፍ ነው።*

*በአቶ መክብብ መጣጥፍ ውስጥ ከተካተቱት ዓበይትና ጠቃሚ ነጥቦች መካከል በርዕሱ ላይ እንደተመለከተው የሰላማዊ ትግል ምንነትና በአገራችን ውስጥ በሚካሄደው ትግል በውጪ ያለው ኢትዮጵያዊ ሚና ምን መምሰል ይኖርበታል? የሚሉት ይገኙበታል። እኔም ከነዚህ ነጥቦች በመነሳት አቶ መክበብ በመጣጥፋቸው ውስጥ ባነሱዋቸው ፍሬ ነገሮች ላይ ያለኝን አመለካከት ለመሰንዘር እሞክራለሁ። እግረ መንገዴም በውጪ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ እስከአሁን ድረስ ያደረገውን ወይም ሊያደርግ ያለወቻለውን አስተዋፅኦ፣ የሃይል አሰላለፍ፣ የፖለቲካና የአርእዮተአለም አመለካከትን፣ በተለይም ጥቂት ፅንፈኞች የሚያራምዱትን የጥላቻና የቂም በቀል ፖለቲካ ስልት ለመቃኘት እሞክራለሁ። ከዛ በፊት ግን እስካሁን ድረስ የነበረውን የስልጣን ርክክብ /መንጠቅና መነጣጠቅ/ በአገሪቱ ላይ ያስከተለውን እልቂትና የደም መፋሰስ ለመጠቆም እሻለሁ።*

*አቶ መክብብ የሰላማዊ ትግል አጠቃላይ ዓለምአቀፋዊ መንፈስ፣ ይዘትና ትርጉም በተለያዩ ተጨባጭ ሁኔታዎች ውስጥ ከተስተዋሉት ክስተቶችና ተሞክሮዎች ጋር እያገናዘቡና ከታሪክ እያጣቀሱ በተለይም በዚህ መስክ አንጋፋ ተዋንያንና በዚሁ የትግል ስልት ፈርቀዳጅ የሆኑት እንደነ ጋንዲ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግና የመሳሰሉትን ዋቢ በማድረግ በሚገባ የገለፁት ስለሆነ ከተባለው ውጪ ብዙ የምለው አይኖረኝም። ስለሆነም አሁን ላተኩርበት የምፈልተገው የዚህ ዓይነቱ የትግል ስልት አገራችን ባሁኑ ወቅት ከምትገኝበት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የትምህርትና የባህል እድገት ደረጃ አንፃር ሲታይ በሚኖረው ወሳኝ ሚና ላይ የሆናል።*

*ያለፈውን ታሪካችን ስንመለከት ይነሱ የነበሩት አመለመግባባቶችና የ ‘ስልጣን ይገባኛል’ ጥያቄዎች ይፈቱ የነበሩት በውይይትና በሰላማዊ መንገድ ሳይሆን*

በጦርነት እንደነበር አይዘነጋም። ህዝቡ ሲከፋው አቶ መክብብ እንደሚሉት "ነፍጥ ከማንሳት" የተሻለ ምርጫ ኑሮት አያውቅም። ገዥዎቹም ይገባናል የሚሉትን ስልጣን ለመንጠቅ ወይም የግዛት አድማሳቸውን ለማስፋት "ምታ ነጋሪት ክተት ስራዊት" እያሉ በሚጭሩት ጦርነት ውስጥ ህዝቡን ከመማገድና እርስ በርሱን ከማፋጀት በቀር መቸም ጊዜ የሰከነ አስተዳደርና የተሻለ አመራር ሰጥተውት አያውቁም እንደ እውነቱ ከሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ በረጅም ታሪኩ ውስጥ ገዥዎች እንጂ መሪዎች ኑሮውት አያውቅም እነዚህም ፈላጭ ቆራጭ ገዥዎች የስልጣን መንበራቸውን የሚረካከቡበት ወይም በትረ መንግስታቸውን የሚነጣጠቁት ቀደም ሲል ለማለት እንደሞከርኩት እልቂትና የንብረት መውደምን ባስከተለ መልኩ ነበር። ግጭትና ፍልሚያ የሚካሄደው በንጉሶችና ራሶች መካከል ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ግልገል መኳንንት ማለትም ደጃዝማቾች፣ ፊታውራሪዎች፣ አበጋዞች፣ ምስለኔዎች፣ መልከኞች፣ ጭቃሹሞችና የጎበዝ አለቆች መካከል ጭምር ስለነበር በዚሁ ሳቢያ በህዝቡ ላይ ይደርስ የነበረው ነውጥና መታመስ በዛው መጠን የበዛና የተደራረበ ነበር።

ብዙ ሩቅ ሳንሄድ አንድና ሁለት ብዛም ቢል ሶስት ትውልድ ያህል መለስ ብለን ብንመለከት ስልጣን ለመረካከብ /ለመነጣጠቅ/ ይደረጉ የነበሩት የእርስበርስ ጦርነቶችና በዚህም ሳቢያ የደረሰው ጥፋት በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ይህም አጤ ምኒሊክ አልጋቸውን ለልጅልጃቸው ለልጅ እያሱ በሰላም ለማስተላለፍ ካደረጉት ያልተሳካ ሙከራና በሃላም ከንግስተነገስታት ዘውዲቱ ወደ አጤ ሃየለስላሴ ከተደረገው የዘውድ ርክክብ በስተቀር /የሰገሌ ጦርነትና ልሎች መለስተኛ ግጭቶች እንዳሉ ሆነው/ ሌላው ከዛ በሷላ ለተደረገው የስላጣን ርክክብ ሁሉ ብዙ መስዋእት ተከፍሎበታል። ለዚህም በአጤ ሃይለስላሴ ጊዜ የተደረጉትን የመንፈንቅለ መንግስት ሙከራዎች ፣ ህዝባዊ አመፆች፣ ብሄራዊ ትግሎችና በሃላም የርሳቸውና የደርግን መንግስት ለመገልበጥ የተደረጉትን ያጤኗል።

የስልጣን ወይም የመብት ጣያቄ በተነሳ ቁጥር መልሱ ጦርነት ብሎም እልቂትና የንብረት መውደም ነበር። ይህም ሊሆን የቻለው በመሪዎቹ እኩይነት ብቻ ሳይሆን ያለመግባባትን በሰላም የመፍታት ልምድና የመቻቻል ባህል ማጣት፤ ስልጣንን በሰላማዊ መንገድ ለመረካከብ የሚያስችሉ ተቋማት ያለመኖርና እነዚህን ሊመራና ሊያዳብር የሚችል ስልጡን ማህበረሰብ ያለመመስረት እንደሆነ የሚያጠያይቅ አይመስለኝም። አሁንም እነዚህና አስፈላጊ የሆኑትና ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች ስላልተሟሉ ያምንመኘውና በጉጉት የምንጠብቀው እኩልነት፣ ዲሞክራሲና ፍትህ የሰፈነበት ህብረተሰብ፣ የፈረጠመ ኢኮኖሚና መልካም መስተዳድር መዘርጋት አይቻልም።

ባሁኑ ወቅት አንዳንድ ድርጅቶችና ደጋፊዎቻቸው እንደ ሚሹት ስልጣንን ባቋራጭ መንገድ ማለትም በትጥቅ ትግል ወይም 'በብርቱኳንና በብጫ አመድ' ወደ ስልጣን ኮርቻ ለመውጣት መሞከሩ ሳይሆን ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው የሰላማዊ የስልጣን ሽግግር አዋላጅ የሆኑትን እሴቶች እውን እንደሆነ በሚደረገው ጥረት ላይ መረባረቡ አማራጭ የሌለው እንደሆነ በአንክሮ ሊጤን ይገባዋል።

በጣም የሚገርመው ግን ዛሬም ካለፈው ጥፋታችን አለመማራችንና አሁንም የሚካሄደው ትግል እንደምንም ብሎ ወደ ስልጣን ለመውጣት እንጂ የትግሉ ሰላማዊ ያለመሆን የሚያስከትለው ሰበብ የሚያሳስባቸው ጥቂቶች መሆናቸውን ነው። ይልቁንም ባሁኑ ወቅት ስልጣን ለመንጠቅ ወይም ላለመንጠቅ በሚደረገው ያጥፍቶ መጣፋት ዘመቻ ተሳታፊ የሆነው ልሂቅ ካለፈው የቅርብ ታሪኩ ሊማር ያለመቻሉን ነው።

ትላንት "የቀይና ነጭ ሽብር" ጎራ ለይቶ ያደረገው የእርስበርስ መጨፋጨፍ፣ በአድሃሪና ተራማጅ ሰፈር ተከፋፍሎ ያካሄደው ፍልሚያ የብሄርና ህብረብሄር ቡድን መስርቶ የከፈራቸው ጦርነቶች አገሪቱ እጅጉን ወደሃላ እንደጎተታታት ማየት ተስኖት አሁንም ወደሌላ ጥፋት እያመራ መሆኑን ነው።

ሁሉን አቀፍ የሆነን ዲሞክራሲ መተግበር የህግ የበላይነትን ለማስፈን ብሎም በእኩልነት ላይ የተመሰረተ መልካም መስተዳድር የሚዘረጋውና የሚጠናከረው በሂደት እንደሆነ ብዙዎቻችን በተለይም ተምሪያለሁ የሚለው ክፍል የሚስተው አይመስለኝም።

እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ያለችውን እንስሳ አስተሳሰብ ካልተጋራን በስተቀር 'በተገኘው አጋጣሚ ስንጥቆ በመግባት' ወይም በሚፈጠረው ግርግርና ቀውስ ተጠቅሞ የሚገኝ ስልጣን ወደፊት ይገባኛል ባይ ሌላ ሃይለኛ ሲመጣ የሚታጣ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ለመንጠቅና ላለመንጠቅ በሚደረገው ፍልሚያ ሳቢያ የሚከተለው መዘዝ ምን ያህል እንደሚሆን መስተዋል ይኖርበታል።

ባለንበት ዘመን አንፃራዊ የሆነ ፍትህ፣ እኩልነትና ዲሞክራሲ ሰፍኖ የሚገኝባቸው አገሮችን ስንመለከት አሁን ካሉበት ደረጃ ሊደርሱ የቻሉት ባንድ ቀን ዥምበር ሳይሆን ከብዙ ጊሂ ውጣውረድና ከፍተኛ ጥንቃቄን የጠየቀ የግምባታ ስራ ነው። ይህም ሲባል የእንግሊዝ ፓርላሜንታዊ ዲሞክራሲ ከሚገኝበት ደረጃ ለመድረስ የሰወደበትን 800 ዓመታት አህል /*ከማግናካረታ* መከተብ ጀምሮ/ ይውሰድብን ለማለት ሳይሆን የወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ በፈቀደው መጠነት ሰከን ብለን ያሉትን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖያዊና የሲቪል ተቋማት በሂደት እንዲጎለብቱና እንዲጠናከሩ ጊዜ መስጠቱ አስፈላጊ እንደሆነ ለመጠቆም ያህል ነው።

ለምሳሌ አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ከእርሱ በፊት የነበረውን አስወግዶ ስልጣን ከጨበጠበት ጊዜ ወዲህ ያለውን ብንመለከት ምንም እንኳ የሁሉንም ይሁንታ ባያገኝም አዲስ ህገመንግስት ተረቆ በስራ ላይ ውለዋል። በዚህም መሰረት የተለያየ ቀለምና እምነት የላቸው በርካታ የፖለቲካ ፖርቲዎች ተመስረተው እየተንቀሳቀሱ ናቸው። ራሱ ከሚፈጥራቸውና ከውጪ ከሚሰነዘሩት ችግሮች ገና ያልተላቀቀ ቢሆንም ከድሮው የተሻለና የተለየ የነፃ ፕሬስ አውታር እየተዘረጋ ነው። ገና ብዙ ይቀረዋል ቢባልም ህዝቡ ዴሞክራሲን እየተለማመደ ነው። ይህም ተከትሎ እስከአሁን ድረስ ሶስት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ምርጫ ተካሂደዋል።

በመጀመሪያ ዙር ምርጫ ካንድ ወይም ሁለት በግል ተወዳድረው ከተመረጡት ሌላ የምክርቤቱ መቀመጫዎች በሙሉ የተያዙት በገዥው ፖርቲ አባላት ነበር። ቀጥሎ

በተካሄደው ምርጫ ደግሞ የሌሎች ተቃዋሚ ፖርቲዎች አባላት ተሳታፊ የሆኑበትና ውጤቱም ከመጀመሪያው የተሻለ እንደነበር አይዘነጋም። ለዋቆ በተካሄደው የሶስተኛው ዙር ምርጫም የነበረው ውዝግብ እንዳለ ሆኖ ገዥው ፖርቲ ያገኘው የምክርቤት መቀመጫ ቁጥር ካለፊው በጣም ዝቅ ከማለቱም በላይ በአዲስ አበባና ሌሎች ከተሞች በማያሻማ መልኩ ተሸንፊዋል።

እንግዲህ ይህ አሁን የሚታየው የፖለቲካ ክስተትና ህዝቡ የደረሰበት የንቃተህሊና ደረጃ በቅንነት ለተመለከተው በምንም መልኩ ቢታይ ድሮ ከነበረበት ቢያንስ አንድ እርምጃ ወደፊት ተራምደዋል። ይህም የሆነው ባለፉት 16 እና 17 ዓመታት ውስጥ ከሆነ ለወደፊቱ ካለበት በተሻለ መልኩ በሂደት እየጠራ እንዲሄድ የሰላም ትግሉ ለሌላ ጥቂት ዓመታት ቢቀጥል ጉዳቱ እምን ላይ ነው።

ይህም ስል አሁን ስልጣን ላይ ያለው መንግስት እንዲቀጥል የሚያስችል ፋታ እንዲሰጠው ለመየቅ ሳይሆን በቂ ጊዜ ከተሰጠው የህዝቡ ንቃተ ህሊና ከዳበረ የምርጫ ማስፈፀሚያክፍሎችና ሌሎች ተቋማት እየተጠናከሩ፣ የነፃው ፕሬስ ተሳትፎ እየሰፋ ሲሄድ መራጩን ለማወናበድ የሚኖረው ዕድል ዝቅተኛ ይሆናል፣ መራጩም ያልፈቀደውን የፖለቲካ ፖርቲ አስወግዶ የሚፈልገውን ወደ ስልጣን ለማምጣት የሚያስችልበት ጊዜ ሩቅ አይሆንምና ረጋ ብለን እንጌዝ ለማለት ያህል ነው።

እንደሚታወሰው ባብዛኛው ለይስሙላ ቢሆንም የኢትዮጵያ ህዝብ የምክርቤት “ተወካዮችን” መምረጣ ከጀመረ ወደ 50 ዓመት ሆኖታል። ይህም ያጤውን ፓርላማ፣ የደርጉን ሸንጎና የአሁኑ የተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለመምረዋ የተካሄዱት ምርጫዎችን ያጠቃልላል። በዚህም ሂደት ውስጣ መጠነኛም ቢሆን የቅርጽና የይዘት መሻሻል ታይተዋል። ለምሳሌ ላጤው ፓርላማ ይቀርቡ የነበሩት እጩዎች ከመሳፍንቱ፣ መኳንንቱ፣ ከበርቴውና ባለርስቱ ወገን ብቻ ሲሆን መመዘኛውም የሙያ ብቃትና የስራ ችሎታ ሳይሆን የሀብት መጠንና የትውልድ ሃረግ ነበር። በደርጉም ጊዜ ቢሆን ምንም እንኳ የተካሄዱት ምርጫዎች የተደረገውን የመደብ ሹምሽር ተከትለው የመጡ በመሆናቸው የተወዳዳሪው ዓይነት የጭቁኑ መደብ ያካተተ ቢሆንም አሰራሩ ከበፊቱ የተሻለ አልነበረም። ህዝቡ ለሸንጎ አባልነት በመንግስት /ሰርቶ አደሩ ፖርቲ/ ከተመለመሉት እጩዎች ውጪ መምረጥ አይችልም ነበር። ስለሆነም ባሁኑ ወቅት በስራላይ ያለው የምርጫ ስርአት ከአለፉት ጋር ሲወዳደር አንፃራዊ የሆኑ መሻሻሎችን እንዳሳዩ ይታመናል። በተለይም የሶስተኛው ዙር ምርጫ ካለፉት ጋር ሲነፃፀር የተሻለ የዲሞክራሲ ገጽታ ታይቶበት እንደነበር ብዙዎቹ ይናገራሉ። በዚህም መልኩ ቀጥሎ በሂደት የጎደለው እየተሟላ፣ የጎበጠው እየተቃና እና ያሉትም ተቋማት እየተጠናከሩ ሲሄዱ የሚቀጥለው ምርጫ ካለፉት ሁሉ የተሻለና ውጤቱም አመርቂ እንደሚሆን ተስፋ ይደረጋል።

ነገር ግን ይህ ሳይሆን ቀርቶ ስልጣንን በህዝብ ፈቃድ ሳ ሆን በህዝባዊ አመፅ ባቋርጭ ለመጨበጥ ወይም “ሁለት ባላ ትከል አንዱ ቢሰበር ባንዱ ተንጠልጠል” የሚለውን ቀመር በመጠቀም የሰላሙንና የነውጠኝነት ትግል እያፈራረቁ ለማራመድ መሞከሩ ውጤቱ መሻሻል ሳይሆን ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ይሆናል።

ዲሞክራሲያዊነት ሰፍኖ የህዝቡም መብትና ነፃነት የተሟል የሚሆነው እኛ የምንመራው መንግስት ሲቋቋም ብቻ ነው የሚለው ፈሊጥ ትምክህተኝነትን ከማንፀባረቁም ሌላ አስተሳሰቡ ቧላ ቀርና ምናልባትም እንደነ ዶ/ር ብርሃኑ አባባል "የፈራ ፖለቲካ" ስለሚሆን ባጭሩ መቀጨት ይኖርበታል። እንዲሁም ያንዳንድ የፖለቲካ ፖርቲዎች፣ ስብስቦችና ግለሰቦች ህልምና ምኞት እነሱን ለስልጣን የሚያበቃ ነፃና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ላንዴና ለመጨረሻ እንዲካሄድ እንጂ ለተከታዮ ደንታ ያላቸው አይመስሉም።

*1* አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ስለነዚህ አይነቶቹ ፖለቲከኞች ሲፅፉ ስንዲህ ይላሉ። "… እንደወያኔ በጠመንጃ ሃይል ስልጣን የያዙቱ ብቻ ሳይሆን በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ስልጣ ያገኙትም ጭምር በሌላ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሲሸነፉ ከስልጣን አንወርድም የሚሉ አምባገነኖች መሆን እንደሚችሉ በቅርቡ ኬንያ ውስጥ የተከሰተው ችግር ጥሩ ምስሌ ነው።" ይሉና ቀጠል አደርገውም ' …… ሰፊው የፖለቲካ ልሂቅ አካባቢ ስልጣን ይገባኛል የሚል ግጭት እንጂ ስልጣን የምንገዛበት መንገድ ዲሞክራሲዊ ሊሆን ይገባዋል የሚል እምነት እንዳለው ግልፅ ነው።" በማለት ያጠቃልላሉ። እኔም በዚሁ ጉዳይ ለጊዜው እዚህ ላቁምና ውጪ አገር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ መጫወት ስለሚገባው ምና ወደሚለው የአቶ መክብብ ርስ ልሂድ።

*1* *http//www.kinijitethiopia.org/docs/articles/kinijit_past_present_future_andargachewtsege.pdf*

## "በአገራችን ስለሚካሄደው ሰላማዊ ትግል በውጪ ያለው ኢትዮጵያዊ ሚና"

ስለሚኖረው ሚና ከመነጋገራችን በፊት ስለ ምንነቱና ማንነቱ በቅድሚያ ለማየት ብንሞክር ምናልባት በዚህ ነጥብ ላይ ያለን ግንዛቤ የተሻለ ሊያደርገው ይችል ይሆናል። ምንም እንኳ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ምኞትና ፍላጎት አገሩ በልጽጋ የህዝቡ የኑሮ ደረጃ ተሻሽሎ ህግና ፍትህ የሰፈነበት ሰላማዊ ህይወት እንዲመራ ቢሆንም፣ ይህን እውን ለማድረግ የሚከተለው መርህና የትግል ስልት የተለያየ እንደሚሆን አከራካሪ አይሆንም። ያማ ባይሆን ኑሮ የተለያዩ የፖለቲካ ፖርቲዎችና ፖለቲከኞች ባላስፈለጉንም ነበር። ስለሆነም አንዳንድ ብልጣብልጥና አፈጮሌ ፖለቲከኞች ሊያሳምኑን እንደሚሞክሩት፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በተለይም በውጪ የሚኖረው ሁሉ አንድ አይነት ራኢ ያለውና ተመሳሳይ የፖለቲካ ፍልስፍና የሚከተል አድርጎ መመልከቱ ትክክል አይሆንም።

እንደ አንዳንዶቹ የፖለቲካ ተንታኞች እይታ ከሆነ በውጪ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ/ዳያስፖራ/ ከፖለቲካ አመለካከቱ ፣ ለወደፊቱ ስለምትገነባው ኢትዮጵያ ካለው ግንዛቤ ፣ ከነበረውና አሁን ካለው የፖለቲካ ተሳትፎ ደረጃ አኳያ በሶስት ከፋፍሎ ማየት እንደሚቻል ይታመናል። እነዚህም፦

1. በአገር ውስጥና ካገር ውጪ ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱትን የፖለቲካ ፖርቲዎችና የብሄር እንቅስቃሴዎች የሚደግፈው፣

2. ግልፅ የሆነ የፖለቲካ ፕሮግራምና አላማ ሳይኖረው ፣ ቢኖረውም ግልፅ አድርጎ ያላስቀመጠ ፣ ከየትኛውም አቅጣጫ የሚመጣውን ሃሳብ በጥርጣሬ የሚመለከት ፣ የሚደረገው ሰላማዊ ትግል ተሳታፊ በመሆን ማበረታቻና ገምቢ ሂስ ከመስጠት ይልቅ የሚሰራውን መንቀፍና የተሰራውን ማጣጣል ከዛም አልፎ የጥላቻና የቂም በቀል ፖለቲካ ማራመድ የሚቀናው ክፍል፣

3. እዚህም እዛም ሳይል "እስከ ንአምሮ ለፈጣሪነ እንቁም በባህላዊነ" የሚል ይመስል የሚካሄደውን ትግል በጥሞና፣ በአርምሞና በአንክሮ የሚከታተለው ብዙሃኑ ክፍል ነው። እንግዲህ በዚሁ አመለካከት የምንስማማ ከሆነ የሚቀጥለው ጥያቄ እነዚህ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ሶስት ክፍሎች ማእቀፍ ውስጥ የሚገኙት ተዋንያን ሚና ምን መምስል አለበት? የሚል ብቻ ሳይሆን ተሳታፊዎቹ የሰላሙን ትግል አካል ለመሆን የሚያስችሉዋቸው ቅድመ ሁኔታዎች የትኛዎቹ ናቸው? የሚል ቢታከልበት መልካም ነው።

እንደኔ እምነት አላማችን ምንም ሆነ ምን ወደአቀድነው ግብ ለመድረስ የምናደርገው ጉዞ ሰላማዊ እንዲሆን ፣ በቅድሚያ እስካሁን ድረስ ስንከተለ የነበረውን የትግል ስልት ፣ ባህልና ልምድ እርግፍ አድርገን መተው ይኖርብናል።

ይህም ሲባል በአመለካከታቸው ከኛ በሚለዮት ወገኖች ላይ የምናካሂደው የጥላቻ የሰም ማጥፋትና ያሉባልታ ዘመቻ ፣ በተለይም ተቃዋሚዎቻችንን ይደግፋሉ በምንላቸው ላይ የምንከተለው የማስፈራራትና የማጋጣበር /intimidation and bulling tactics/ ስልት መቆም ይኖርበታል።

ኢትዮጵያዊነት በእኩልነት የምንጋራው መብት እንጂ አንዱ ለሌላው የሚሰጠው ችሮታ እንዳይደለ በመገንዘብ ባሁኑ ወቅት በተለይም ከጥቂት ብልጣብልጦች እንደሚደመጠው ራስን እንደ አንጋፋ ባላገር ሌላው ከጨረቃ እንደመጣ ባዕድ መቁጠሩ የትም እንደማያደርስ መጤን አለበት።

ሌላው ትልቁ ችግር ደግሞ ቅራኔዎችን በውይይት ለመፍታት ያለመቻል ባህልና ለፖለቲካ ባላንጣዎች የሚገባቸውን አክብሮት ያለመስጠት ልምድ ነው። ብዙሃኑ ወይም በፈረንጅኛው አጠራር /The silent majority/ በመባል የሚታወቀው ክፍል የሚከተለው " ከፖለቲካና ከኮሬንቲ ራቅ ማለት ነው" የሚለው የገለልተኛነት አመለካከት ደግሞ ሌላው መሻሻል ያለበት ባህል ይሆናል።

ልብ ብለን ከሆነ አብዛኞቻችን በተገኘውና በሚገኘው አጋጣሚ ለማለት የምንፈልገውን ወይም እንዲነሳ የምንሻውን ነጥብ ራሳችን ከማንሳት ይልቅ ሌላው ቢያነሳልን እንመርጣለን። ይህም በይሉኝታ ላይ የተመሰረተ የመተሳሰብ ባህል ሳይሆን፣ ምናልባት ለሚያምኑበት ነገር በግምባር የመከራከር ባህልና ይገባኛል ለሚሉት መብትም ሆነ ጥቅማጥቅም ፈርጠም ብሎ የመከራከር ልምድ ማጣት ሳይሆን አይቀርም ብየ እገምታለሁ። የዚህ አይነቱ ባህል ማለትም የራስን ወይም የወገን መብትና ሰብአዊ ክብር ለማስጠበቅ በሚደረገው ትግል ቀጥተኛ ተሳታፊ ያለመሆን ፣ ለሚያምኑበት ነገር ሽንጥን ገትሮ ያለመከራከርና የሚፈልጉትን በሌሎች ትከሻ ለማግኘት መሞከር ደካማነትን ከማሳየቱ ሌላ አንዳንድ አፈጮሌና ዋልጌ ፖለቲከኞች ካለምንም ቁጥጥር እንዳሻቸው እንዲፏልሉ እድል መስጠት ይሆናል። ይህንን ካልኩ ዘንዳ ቀደም ሲል ወዳንሳሁት 'በሰላዊ የትግል ሂደት የ *ዳያስፖራው* ሚና' ወደሚለው ልመለስና ይህንኑን አስመልክተው አቶ መክብብ ባነሱዋቸው ነጥቦች ላይ ያለኝን አስተያየት ልስጥ።
በቅድሚያ ግን አንድ ግልፅ እንዲሆንልኝ የምፈልገው ነገር አለ ። ይኸውም አቶ መክብብ "ተባበር" የሚሉት የትኛውን ክፍል ነው? እርሳቸው የ "ማፊያ ቡድን" የሚሉትን መንግስት በመቃወም "የተፈቱት መሪዎቻችን" የሚሉዋቸውን የሚደግፍ? ወይስ የሚደግፈውም ሆነ የሚቃወመውን ሁሉ ያጠቃልላል? እንግዲህ መልሱ የመጀመሪያው ከሆነ አቶ መክብብና እኔ ላለመስማማት ተስማምንተን እዚሁ ላይ እናቆማለን። ነገር ግን ጥሪው ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ማለትም የአቶ መክብብን መሪዎች ለሚደግፈው ፣ ለሚቃወመውና ለገለልተኛው ሁሉ ከሆነ የመልእክቱ ፍሬ ነገር አቶ መክብብ እንዳሉት ".......ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተነሳውን መከፋፈል ፍፁም ወደሀኋ በማለት....." ሳይሆን በዚሁ አንቀፅ ውስጥ ዝቅ ብለው ".....ያለን ልዮነት እንዳለ ሆኖ...." በማለት እንዳስቀመጡት የሚኖሩት የፖለቲካና የርእዮተአለም ልዮነቶች እንዳሉ ሆነው በምንስማማባቸው ነጥቦች ዙርያ በመሰለፍ ወደምንፈልገው ግብ ለመድረስ የምናደርገው ትግል ሰላማዊ መሆን አለበት ቢሆን የተሻለ ይሆናል።

እንደሚታወቀው በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ሰላምና እኩልነት የሰፈነበት ዴሚክራሲ አለ የሚባለው ህዝቦች ያገርን ጥቅምና የወገንን ህልውና በማይጎዳ መልኩ የተለያየ የፖለቲካ አመለካከት ሲኖራቸውና ማንንም ሳይፈሩ እምነታቸውን መግለፅ ሲችሉ እንደሆነ አቶ መክብብም እንደሚያምኑበት እርግጠኛ ነኝ።

በዚህ ከተስማማን ፣ የተለያ አመለካከት ያላቸው ክፍሎች ወደሚፈልጉት ግብ ለመድረስ በሚመስላቸው መልክ ተደራጅተው በሰላማዊ መንገድ እንዲታገሉ ከማበረታት ይልቅ ሁሉንም ባንድ ላይ ጨፍልቆ በአንድ አቅጣጫ ብቻ እንዲሄድ መሞከሩ ፈረንጆቹ እንደሚሉት /one size fits all/ ወይም ባንዱ ልክ የተሰፋን ጥብቆ ለሁሉ እንዲመጥን መጣር ይሆናል። ይህ እንዳይሆን ደግሞ ባሁኑ ጊዜ የሚታየው "ከኛ ጋር ካልተስማማህ በኛ ላይ እንደተነሳህ እንቆጥረዋለን" /either you are with us or against us/ የሚለውን አመለካከት መለወጥ ይኖርበታል።

ለምሳሌ አቶ መክክብ 2 የአቶ ተፈሪ መንግስቴን ፅሁፍ አስመልክተው "…… ሁላችንም ልንስማማበት ወደሚችል እንደ 'H.R 2003' ዓይነት የተቀደሱት ጉዳዮች ላይ በማተኮር …" ይላሉ። እውን አቶ መክብብ እንደሚሉት በውጪ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ሁሉ በ "H.R 2003 ቅዱስነት" እና ትክክለኛነት ያምናል? "H.R 2003" የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅም የሚፃረርና የአገሪቱን ሉአላዊነት የሚፈታተን ነው የሚል ክፍል የለም? ወይስ "ምርጦች" ኢትዮጵያውያን ካመኑበት ሌላውም እንዳመነበት ተቆጥሮ ነው?

---

2 ተፈሪ መንግሰቴ "H.R. 2003: A cause that unifies the Fragmented Diaspora"

ሌላው በጣም ያሳሰበኝና የከነከነኝ አመለካከት ደግሞ የሃይማኖትና የፖለቲካ መቀላቀል ነው። እንደሚታወቀው ባሁኑ ጊዜ በአለማችን ተዘውትሮ እንደሚታየው ፣ በተለይም በአንዳንድ አካባቢዎች እየተከሰተ ያለው የነውጠኝነት ችግር ከዚሁ የመነጨ መሆኑን እየታወቀ ፣ አንዳንድ ፅንፈኛ የሃይማኖት ሰዎች በሚያራምዱት በሃይመኖት የተጠቀለለ የፖለቲካ መልእክት /Religio-political message/ ሳቢያ የተፈጠሩት የቀናኢ ሃይማነተኞች ወይም የፈንድቶ አፈንጂ /Suicide bombers/ ቁጥር የቱን ያህል ከፍ እያለ እንደመጣና እነዚህ ነውጠኞች በሰላማዊ ህዝብ ላይ ያደረሱት ጥፋት ምን ያህል ዘግናኝ እንደሆነ እያወቁ በዚህ መስመር ለመጓዝ መከጀል የጤንነት አይመስለኝም።

በእርግጥ አቶ መክብብ እንደሚሉት የሃይማኖት መስበክያ ቦታዎች “የኢትዮጵያ ትንሳኤ” መስበክያ ጭምር እንደሆኑ የማምንበት ብሆንም ፣ እነዚሁ ቦታዎች እንዱን ክፍል የሚመሰገንባቸውና ሌላው የሚወገዝባቸው ፣ የሃይማኖት ሰዎች በተለይም የእምነት አባቶች ሃይማኖትን እንደ መሳሪያ በመጠቀም አንዱን ፖርቲ ደግፈው ሌላውን የሚኮንኑበት እንዲሆኑ የሚደረገው ሙከራ ግን አጥብቄ እቃወመዋለሁ።

አሁንም አቶ መክብብ ትንሽ ከፍ ብለው “ወደአገራችን ታሪክ ስንመለስ ደግሞ ጀግናው አቡነ ጴጥሮስን እናገኛለን ጣሊያን አገራችንን ወርሮ ህዝቡ ሰጥ ለጥ ብሎ ስንዲገዛላቸው አቡኑን ለመጠቀም ቢሞክርም “እንኳን ህዝቡ ምድሪቱ ላንተ ብትገዛ ውጉዝ ትሁን፡ በማለት ለነፃነት መቆም የሃይማኖት ግዴታቸው በሆኑን የህይወት መስዋዕትነት በመክፈል የመሰከሩ ናቸው” ብለዋል።

የአቡኑ ጀግንነትና ቆራጥነት አጠያያቂ ስላልሆነ በዚሁ ላይ የምጨምረው የለኝም። ሆኖም ግን ከአባባሉ በስተጀርባ ሊተላለፍ የተፈለገ መልእክት ያለ ስለመሰለኝ እንዲሁ ላልፈው አልፈለግኩም።

ምንም እንኳን አቶ መክክብ አንዱ ናቸው የምልበት ምክንያት ባይኖረኝም አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግስት እንደባዕድ ወይም ቅኝገዥ የሚመለከቱት ክፍሎች እንዳሉ አውቃለሁ ። ይህም ያልኩበት ምክንያት ኢትዮጵያ ላጭር ጊዜም ቢሆን በቅኝ አገዛዝ ስር በነበረችበት ወቅት የተደረገው ያርበኝበት ትግል አሁን ከሚካሄደው የእርስ በርስ የፖለቲካ ሽኩቻ ጋር ለማመሳሰል የሚደረገው ሙከራ ስላሳሰበኝ ነው።

አቡነ ጴጥሮስ በአብነት የተጠቀሱበት ምክንያት የወቅቱ ጳጳሳት በተለይም “የግዞት ሲኖዶስ” በመምራት ያሉት አበው ”ምድሪቱ አሁን ላለው መንግስት ብትገዛ ውጉዝ ትሁን” እንዲሉና ባንፃሩም ያገሬው ህዝብ ለተቃዋሚው ፖርቲ /ፖርቲዎች/ ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛ ቡራኬ እንዲሰጡ ታስቦ ከሆነ አባባሉ ሚዛናዊነት የጎደለው ነው እላለሁ። ለነገሩማ ለማለት ያህል ይባል እንደሆን ነው እንጂ አወጋገቹ ቢያወግዙም እንደ አቡነ ጴጥሮሱ ጊዜ ከየከተማው በሚፈልገው ያርበኛ ብዛት የጎጃም፣ የቤጌምድር፣ የሸዋና የትግራይ ተራራና ሸንተረሮች ይጨናነቃሉ ብየ አልገምትም ። ስለሆነም ጊዜው በየፀሎት ቤቱ እየተኮለኮሉ አንዱ ሌላውን የሚኮንንበት ፣ የማይፈቅዱትን ከገፅምድር እንዲያጠፋው

የሚፀለይበት፣ የኡኡታ ኮሚቴ እያቋቋሙ የሚጨጩሁበትና ሲያመችም "ፋኖ ተሰማራ" እያሉ በመዘመር ህዝብን የሚያምሱበት ሳይሆን ፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች ማእቀፍ ውስጥ ያለውም ሆነ ከዚያ ውጪ ያለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ በአገሩ ጉዳይ እኩል እንደሚገባውና በተለይም ወቅታዊ ከሆኑት ገዥ ጉዳዮች ውስጥ የተፈለገውን ደግፎ ያልፈቀደውን የመቃወም ከሌላው ያላነሰ መብት እንዳለው ተቀብሎ አብሮ መስራት የሚያስፈልግበት ነው።

መረሳት የሌለበት በቁጥር ጥቂት ቢሆኑም እንደድሮው አሁንም የእኩልነቱ ጉዳይ የማይዋጥላቸው ወገኖች እንዳሉ ነው። ይህም ሞኝነትን የሚያዋስን ገራገርነት3 የሚያጠቃቸውና በምንአህሎኝነት የተወጠሩት ትምክህተኞችን ይመለከታል።

ለዚህም ነው በሰላም አብሮ ለመኖርም ሆነ የሰላማዊ ትግል በጋራ ለማካሄድ የሚቻለው አንዱን ዜጋ እንዲአንጋፋ ሌላው እንደባዕድ ወይም ሁለተኛ ዜጋ በመመልከትና በማናናቅ ሳይሆን ፣ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፈለገውን የፖለቲካ ፓርቲ ፣ ገዥውን ፓርቲ ጨምሮ ፣ የመደገፍና የመቃወም መብት እንዳለው በፀጋ ተቀብሎና ተከባብሮ ለመኖር የሚያስችል ሁኔታ ሲፈጠር በቻ ነው የሚባለው።

ይህም ካልኩ በሃላ መነሻ ወደሆነኝ ነጥብ ማለትም በውጪ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ 'በሚካሄደው ሰላማዊ ትግል ውስጥ ስለሚኖረው ሚና' ወደ ሚለው ነጥብ በመመለስ በማጠቃለያ መልክ አንዳንድ ነጥቦችን አነሳና ሃሳቤን በዚሁ ለመቋጨት እሞክራለሁ።

በመሰረቱ በውጪ ነዋሪ የሆነው ኢትዮጵያዊ ሁሉ /በትውልድ/ዜግነት/ ካገር ውጪ እስከኖረ ድረስ የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መብት ስለማይኖረው አገር ቤት ውስጥ ባለው እንቅስቃሴ በተለይም በሚካሄደው ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ዙሪያ የሚጫወተው ሚና ከድጋፍ ሰጪነት የሚያልፍ አይሆንም ። የሚሰጠውም ድጋፍ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ደግሞ የድጋፉ አይነት፣ መጠንና የሚሰጥበት ወቅት ድጋፍ ሰጪው በሚፈልገው መንገድ ሳይሆን ለድጋፍ ተቀባዮ በሚስማማውና ለመቀበል ዝግጁ በሆነበት ጊዜ ሲሆን ነው።

ይህ ሳይሆን ቀርቶ ማለትም የሚደረገው እገዛ ታጋዡን ሳይሆን አጋዡን የሚጠቅም መስሎ ከታየ ግን ፣ አጋዡ የሚኖረው ሚና አሉታዊና አፍራሽ ይሆናል።

---

*3 ገራገሮች ፣ ስልም የኢትዮጵያ ህዝብ ይህን ያህል ሚሊዮን ነው ሲሏችው "አረ! ምናምንቴውንም ቆጥራችሁት እነደሆን ነው እንጂ እኛስ አምስት መቶም አንሞላ" ያሉትን ባለቴትና የመሳሰሉትን ለማለት ነው።*

እውቀትም ሆነ ችሎታ ሁለት ገፅታዎች ስለሚኖሩት ውጪ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ በተለይም ምሁሩ ክፍል ዲሞክራዊያዊ ስርአትን ለመገንባት የሚደረገው ግስጋሴ የማፋጠን ወይም ወደሃላ የመጎተት ሚና እንደሚኖረው መዘንጋት የለበትም ። በዚህ አኳያ እንደምሳሌ ሊጠቀሰወ የሚችለው በኢኮኖሚ በገፉት አገሮች ውስጥ የሚኖረው የፖለቲካ ልሂቅ /The vocal Diaspora/ አልፎ አልፎ ሲያደርግ እንደሚታየው  በአገር ውስጥ በሚንቀሳቀሱት የፖለቲካ ፖርቲዎችና ፖለቲከኞች መካከል ያሉትን ውጥረቶች በማርገብ ፋንታ እንዲጦዙ በማድረግ ፣ ፖርቲዎቹ እንዲጠናከሩ ድጋፍ ከመስጠት ይልቅ የተፈጠሩትን መለስተኛ አለመግባባቶች እንዲጋሸቡ የሚያደረገው ሙከራ ነው።

ከዛም አልፎ ያሉትን ውጥን ስራዎች በማጠንከር ፋንታ ጅምሮችን እያዳከመ በምትካቸው አዳዲስ ተቋማትን በራሱ አምሳል ፈጥሮ ስልጣን ለመረከብና ከባህር ማዶ ሆኖ አመራር ለመስጠት እየቃጣው እንደሆነ ከድርጊቱ መገንዘብ ይቻላል።

ስለዚህ ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት በመጀመሪያ ደረጃ መጤን ያለበት ይህ ከውጪ ሆኖ የትውልድ አገሩን ለመርዳት ፈቃደኛ የሆነው ክፍል የተሳትፎው ወሳኝነት ቢኖረውም በደጀንነት እንጂ ቀጥተኛ ወይም ግንባር ቀደም መሪ ያለመሆኑ ጉዳይ ነው። በዚህ ግንዛቤ ከተስማማን ፣ ድጋፍ ሰጪው ክፍል አመራርን ከመስጠት ውጪ ብዙ ሊያደርገው የሚችል የሞራል የቁሳቁስና የሙያ አስተዋፅኦዎች ከመኖራቸውም ሌላ በሚካሄደው የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴ ውስጥ ሊጫወት የሚችለው ሚና ከፍተኛ እንደሚሆን አያጠያይቅም ። በዚህም መሰረት በአገር ውስጥ የሚካሄደውን ግንባታ ስራ ለማገዝ መደረግ ከሚገባቸው አስተዋፅኦና ድጋፍ ጥቂቶቹን ከዚህ በታች ለመጠቆም እሞክራለሁ፦

- በመዋዕለ ንዋይና የሰለጠነ የሰው ሃይል አቅርቦት እጥረት አኳያ ያለውን ችግር ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት ተሳታፊ መሆን፣
- የሲቪልና የሙያ ማህበራት መሪዎችና ሙያተኞች የትምህርት ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉና የተሻለ የስራልምድ እንዲያካብቱ የሚያስችሉ ሰሚናሮችና አውደጥናቶች ማዘጋጀት፣ አቅም ሲፈቅድም በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ ሄደው ያጭርና የረጅም ጊዜ ትምህርትና ስልጠና እንዲከታተሉ መርዳት፣
- ብቃቱ ያለቸው ምሁራንና ሌሎች ባለሙያዎች ባማካሪነት /Consultant/ ደረጃ በየሙያ መስካቸው አስተዋፅኦ የሚያደርጉበት ፕሮግራም መዘርጋት፣
- *4* <u>ለጋሽ አገሮችና</u>  አለም አቀፋዊ የልማት ድርጅቶች ኢትዮጵያ በምታደርገው የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካና ያቅም ግንባታ ስራ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማግባባት/Lobbying/

- የሚሰጠው ድጋፍ መሰፈርቱ ከፓርቲዎችና ፖለቲከኞች ጋር ያለውን 5 <u>የግል ግንኙነት</u> ማለትም የሰፈር/መንደር ልጅነት የብሄር ወይም የስጋ ዝምድና ሳይሆን ፣ ፓርቲዎች ወይም የፓርቲ መሪዎች በሚኖራቸው የአላማ ጥራት፣ ለህዝብ ካላቸው ፍቅርና ታማኝነት አንፃር እንዲሆን መጣር፣

- የሚደረገው ተቃዉሞ በአመራር ላይ ላሉት መሪዎች ያለንን 6 <u>የደፈና ጥላቻ</u> መግለጫ ሳይሆን መሪዎች ከሚሰነዘረው ገንቢ ሂስና ማበረታቻ ትምህርት አግኝተው እንዲሻሻሉ ለማድረግ መሆኑን መገንዘብ፣

- በውጪ ያሉት ድረ ገፆች ፣ የሬድዮ ጣብያዎች ፣ መፅሄቶችና ጋዜጦች በተለይም የነዚህ መገናኛ ብዙሀን አዘጋጆች ፣ ሃያሲያንና ፀሁፍ አቅራቢዎች /contributors/ የሚያቀርቡዋቸው ፕሮግራሞች፣ ፅሁፎችና ውይይቶች መልእክት አንዱን ከስልጣን አውርዶ ሌላ ለመተካት ሳይሆን ፣ የህዝቡ ንቃተህሊና ከፍ እንዲል ፣ የፖለቲካ ልምዱ እንዲዳብር፣ ለስልጣን ሽግግር አስፈላጊ የሆኑት ተቋማት እንዲጠናከሩ በአገር ውስጥ ያለው ታዳጊው ነፃ ሚዲያ እንዲስፋፋና ህዝቡ አንዱን ፓርቲ ጥሎ ሌላውን የሚያነሳው በድምፅ ማጉያ ሳይሆን በድምፅ መስጫ ሳጥን መሆኑን በውል እንዲጨን የማድረግ ከፍተኛ ሃላፊነት እንዳለበት መገንዘብ።

በመጨረሻም በውጪ ያለው ኢትዮጵያዊ በተለይም በኢኮኖሚ በገፉትና ሊብራል ዴሞክራሲን ስርአት በሚያራምዱት አገሮች ውስጥ የሚኖረው ክፍል /7 በፓርቲ ተደራጅተው በትረ መንግስት ለመጨበጥ የሚንቀሳቀሱትን ሳይጨምር/ ካለው ልምድና ገጠመኝ በመነሳት ለውድ አገሩ ካደረገው፣ በማድረግ ላይ ካለውና ለወደፊቱ ከሚያደርገው የሞራልና የቁሳቁስ ድጋፍ ሌላ ፣ ቀደም ብየ እንደጠቀስኩት በአገርቤት የተጀመረውን የዴሞክራሲ ግንባታ ለማፋጠን ፣ ባጠቃላይም ህዝቡ ከነበረው ፊውዳላዊ አስተሳሰብ እንዲላቀቅ በተለይ ደግሞ በፖለቲካ፣ በሲቪልና ወታደራዊ ተቋማት ውስጥ ያለው የፀጥታ አስከባሪና የመንግስት ሰራተኛ /Military & Civil Servants/ የወቅቱ መንግስት /Government of the day/ አሽከርና መገልገያ ሳይሆን፣አገልጋይነቱና ታማኝነቱ ለህዝብና ለህገ መንግስቱ መሆኑን እንዲገነዘብ ለማድረግ በሚደረገው ዘመቻ ከፍተኛ ሚና ሊጫወት እንደሚችል መታወቅ አለበት።

---

4 ዲያስፖራው' በችግር ላይ ያለውን ህዝን ይበልጥ እንዲቸገር ማእቀብ እንዲያደርጉበት ለጋሽ አገሮችን ከመማጠን ይልቅ ድጋፋቸውን እንዲሰጡት ማግባባት ግዴታው ይሆናል።

5 & 6 እዚህ ላይ ለማለት የፈለግኩት ጥሩ ሰራ ተሰራም አልተሰራ የሚሰራውን ክፍል ስለጠሉ ብቻ ሁለሌ መቃወም ወይም በሚኖረው ብቃት ሳይሆን ባሉት ግላዊ ምክንያቶች አንዱን ፓርቲ ስለወደዱ የፓርቲው መሪዎች 'ባጎነፈናቸው' ቁጥር ማሰነጠሰ ሚዛናዊነት ጎደለው ዳኝነት እንደሆነ ለማሰገንዘብ ነው

7 በዚህ መልክ የተደራጁት ክፍሎች አስተዋፅኦ አያደርጉም ወይም አያደርጉም ለማለት ሳይሆን ፣ ለየት ያለ ግንና አላማ ሰላላቸው የሚኖራቸውም አስተዋፅኦ ከተራው ዜጋ (በድርጅት ያልታቀፈው) የተለየ መሆኑን ለመጠቆም ነው።